# ይኸን ያውቁ ኖሯልን !

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የሀገሪቱን እምቅ አቅም በመግራት ዘመናዊ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ሆና በሥልጣኔ ጉዳና እንድትረማመድና የአካባቢ ጐረቤት ሃገሮችም ከዚህ የኤሌክትሪክ ኃይለ ሃብት ተጋሪ እንዲሆኑ በር የሚከፍት የተፈጥሮ ፀጋዋን ጥቅም ላይ የማዋል እቅድ ይዛ መንቀሳቀስ ጀምራለች፡፡

የዚህ ግዙፍ ትልም እውንነት ብዙ የኢንቨስትመንት ፍሰትና መዋዕለ ነዋይ የሚጠይቅ በመሆኑ በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን ተጠቃሚ በማድረግ የሚያሳትፍ ውጥን ተነድፏል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ፓወርን ለማስፋፋት እያደገ ላላው ሰፊ እንቅስቃሴ የሚያስፈልገውን የፋይናንስ አቅም ለማጉልበት በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ብቻ የተፈቀደ የቦንድ ሽያጭ በገበያ ላይ አውሏል፡፡

ይህ የሚሊንየም ቦንድ በሚል ስያሜ የታወቀው ኮርፖሬት ቦንድ ዝቅተኛ ዋጋ 500 የአሜሪካን ዶላር ሲሆን ተጨማሪ ቦንድ መግዛት ለሚፈልጉ ግን የብዛት ገደብ የለውም የቦንዱ የጊዜ ገደብ 5፣ 7 እና 10 ዓመት ሆኖ ቦንዱ የሚያስገኘው ወለድ በቅድም ተከተል 4% ፣ 4.5%፣ 5% ወለድ በየዓመቱ ባንኩ ይከፍላል፡፡

ቦንዱ የሚከፍልበት ጊዜ የቦንዱ የጊዜ ገደብ ሲያበቃ ሆኖ ወለድ ግን በየዓመቱ ይከፈላል፡፡ መንግሥት ለቦንዱ ሙሉ ዋስትናን የሰጠ ሲሆን በተጨማሪም ቦንዱ ሀገር ውስጥ ለሚጠየቅ ብድር በዋስትናነት ከማገልገሉም በላይ ከቦንዱ ግዥ የሚገኝ የወለድ ገቢ ከግብር ነፃ ነው፡፡ የወለድ ክፍያን በተመለከተም በውጭ ምንዛሪ ወይም በወቅቱ በሚኖረው የውጭ ምንዛሪ ተመን ታስቦ በብር በገዥው ምርጫ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ የቦንዱ የጊዜ ገደብ ሲደርስ ገዥው በሚፈልገውና በመረጠው መንገድ በውጭ ምንዛሪ ሊከፈለው፣ በውጭ ምንዛሪ በሚከፍተው ሂሳብ ገቢ ሊደረግለት ሌላ ተጨማሪ ቦንድ ሊገዛበት ወይም ከውጭ ለሚያስገበባቸው እቃዎች ክፍያ ለመፈፀም ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

ቦንድ የሚገዙ ሰዎች በቀጥታ ወይም በውክልና መግዛት ይችላሉ፡፡ ቦንዱን በቀጥታ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወይም በየሀገሩ ከሚገኙት የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ሚስዮኖች መግዛት ይችላል፡፡

## *ታዲያስ የእርሶ ሚና ምን ይሁን ?*

## *ጉብዝ !*

ይህ ወቅታዊ ጥሪና መልእክት ሀገርንና ወገንን ለመጥቀም ፍላጐቱ ኖሮን መንገዱን እስካሁን ላልታየን ወገኖችና እንዲሁም መሳ ለመሳ ራሳችንንና ቤተሰቦቻችንን ለመጥቀም ለምንፈልግ ሁሉ መልካም አጋጣሚነውና በሀገርና በወገን ፍቅር ስሜት አጋርነታችንን እንግለፅ የተፈጥሮ ድልብ ሀብታችን ወገናችንና ሃገራችንን ወደ ዘመናዊ የሥልጣኔ መድረክ እንዲያሸጋግራት ታሪክ ከፊታችን ተደቀነብን ምርጫ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት እንሽቀዳደም! እንረባረብ!

*ገንዘብ ገንዘብ ገንዘብ ያለው ያውጣ! ይሥራ ያሠራበት!*
*ኢትዮጵያ እንድታድግ ሁሉም እንዲያልፍለት !*

*ለተጨማሪ ማብራሪያና ተሳትፎ* !
አቶ ሙሉጌታ ከሊል /አማካሪ/
ስልክ ቁጥር 202 274 4555
e-mail. mulugeta@ethiopianembassy.org
3506 International Drive, N.W.
Washington D.C. 20008